ይህ የመረጃ ቅጽ በሁሉም የካሊፎርኒያ ካውንቲዎች ውስጥ ለሚገኙ መራጮች የተዘጋጀ ነው፤ በዚህ ውስጥ **የማይካተቱ** ካውንቲዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡ Amador, Butte, Calaveras, El Dorado, Fresno, Los Angeles, Madera, Mariposa, Napa, Nevada, Orange, Sacramento, San Mateo, Santa Clara, እና Tuolumne ናቸው።

# የመራጭነት መብቶችዎን ይወቁ

ASIAN AMERICANS ADVANCING JUSTICE
ASIAN LAW CAUCUS

## ድምፅ ለመስጠት ዝግጁ ስለመሆን

በአንድ ምርጫ ላይ ድምፅ ለመስጠት፣ በቅድሚያ በመራጭነት መመዝገብ አለብዎት! በመራጭነት መመዝገብ የሚችሉት የሚከተሉትን መስፈርቶች ሲያሟሉ ብቻ ነው።

- የአሜሪካ ዜጋ ከሆኑ፤
- የካሊፎርኒያ ነዋሪ ከሆኑ፤
- በምርጫው ዕለት ዕድሜዎ 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፤
- ከባድ ወንጀል ፈጽመው ጥፋተኛ በመባልዎት በአሁኑ ጊዜ በማረሚያ ቤት ውስጥ ካልሆኑ ወይም አመክሮ ላይ ካልሆኑ፤
- ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል "የአእምሮ ጤና ብቃት እንደሌለዎት" በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠ።

### በምርጫው ለመሳተፍ ቀደመ ሲል ተመዝግበዋል?

የመራጮች ምዝገባ መረጃዎን ያጣሩና ያረጋግጡ። ይህን ድረ ገጽ በመጠቀም የሚከተሉትን መረጃወችም ትክክለኝነታቸውን ያረጋግጡ፡ voterstatus.sos.ca.gov

- የመልእክት መቀበያ አድራሻዎትን ትክክለኝነት ያረጋግጡ።
- ከካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እንዲችሉ የሚጠቀሙበትን ትክክለኛ የኢሜይል አድራሻ ይጥቀሱ
- የሚተረጎሙ የምርጫ ሰነዶች በአካባቢዎ የሚገኙ ከሆነ ለትርጉም የሚመርጡትን ቋንቋም ይጠቁሙ

### ለ2020 ሃገራዊ ምርጫ መመዝገብ ይፈልጋሉ?

በምርጫው ለመሳተፍ ከሰኞ፣ ኦክቶበር 19 ጀምሮ  በሚከተሉት መንገዶች መመዝገብ ይችላሉ፡

- በድህረ ገጽ አማካይነት፡ registertovote.ca.gov፤
- በአካባቢዎ ወደ ሚገኝ DMV፣ ፖስታ ቤት፣ ቤተ መጻሕፍት ወይንም በካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት፤ በመሄድ ወይንም
- በስልክ ቁጥር (800) 345-8683 በመደወል የመራጮችን የምዝገባ ቅጽ በመጠየቅና እስከ ኦክቶበር 19 ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ፖስታ ቤት እንዲደርስ በማድረግ። የቅድሚያ ክፍያ ስለተደረገበት ፖስታውን ለመላክ ቴምብር አያስፈልገውም!

### ከኦክቶበር 19 በኋላ ለመመዝገብ ብፈልግ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ችግር የለዉም! "የምርጫው ቀን ድረስ የሚደረገውን የመራጮች የምዝገባ ሂደት" በመጠቀም እስከ ምርጫው ቀን ድረስ መመዝገብና ድምፅ መስጠት ይችላሉ።

አማራጭ 1፡ በተመሳሳይ ቀን ለመመዝገብና ድምፅ ለመስጠት በአካል መገኘት ይኖርብዎታል።

| | |
|---|---|
| ከኦክቶበር 19 እስከ ኖቬምበር 2 | ወደ ካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት በመሄድ ይመዝገቡና ድምፅ ይስጡ።<br><br>የምርጫ ጽ/ቤትዎን አድራሻ ለማግኘት ይኽን አስፈንጣሪ ይጫኑ፡ sos.ca.gov/county-elections-offices |
| ኖቬምበር 3 (የምርጫ ቀን) | በካውንቲዎ ውስጥ ወደሚገኝ የትኛውም የምርጫ ጣቢያ በመሄድ መመዝገብና ድምፅ መስጠት ይችላሉ። በሁሉም የአካባቢ ውድድሮች ላይ ድምፅ ለመስጠት ከፈለጉ፣ ከቤትዎ አቅራቢያ ወደሚገኝ የምርጫ ጣቢያ ይሂዱ። የአካባቢዎን የምርጫ ጣቢያ አድራሻ ለማወቅ ይኽን አስፈንጣሪ በመጫን አድራሻዎን ይፃፉ፡ sos.ca.gov/elections/polling-place/<br><br>ወደ ካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት ስልክ ደውለው ወደ የትኛው የምርጫ ጣቢያ መሄድ እንዳለብዎት መጠየቅም ይችላሉ። |

አማራጭ 2፡ በመራጭነት ካልተመዘገቡና ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያ ለመሄድ ካልቻሉ፣ የካውንቲዎን የምርጫ ጽ/ቤት በስልክ በማነጋገር "በፖስታ አማካይነት ከርቀት ድምፅ የመስጫ ዘዴ" በመጠቀም በርቀት እንዴት መመዝገብና ድምፅ መስጠት እንደሚችሉ ይጠይቁ።

## የካሊፎርኒያ የ2020 ጠቅላላ ምርጫ

| | |
|---|---|
| **ኦክቶበር 5/2020 ጀምሮ ሲሆን** | የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ለሁሉም የተመዘገቡ መራጮች የሚላክበት ቀን |
| **ማክሰኞ፣ ኦክቶበር 6/2020 ነው** | የድምፅ መስጫ ሳጥኖች የሚከፈቱበት ቀን፡ ደግሞ |
| **ቀን፡ ኦክቶበር 19/2020 ነው** | በምርጫው ለመሳተፍ የመጨረሻው የምዝገባ ቀን |
| **ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 3/2020 (የምርጫ ቀን)** | የምርጫው የመጨረሻ ድምፅ መስጫ ቀን ሲሆን አብዛኞወቹ ካውንቲዎች ከኦክቶበር 31/2020 ጀምሮ መራጮች አስቀድመው መምረጥ የሚችሉበትን ሁኔታ አስተካክለው ይጨርሳሉ። |

# ድምፅ መስጠት የሚቻልባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው? ድምፅ ለመስጠት የሚችሉበት የተለያዩ አማራጮች አሉዎት!

## እቤትዎ ሆነው ድምፅ መስጠት ይችላሉ

እስከ ኦክቶበር 19 ድረስ ከተመዘገቡ፣ የድምፅ መስጫ ወረቀት በመልእክት መቀበያ (በፖስታ ቤት) ውስጥ የሚላክልዎት ሲሆን የምርጫ ወረቀቱን እንዴት እንደሚሞሉና እንደሚመልሱ የሚያስረዱ መመሪያዎችም ከምርጫ ቅፁ ጋር አብሮ ይደርስዎታል። ወደ ምርጫ ጣቢያ ሳይሄዱ በምርጫው ለመሳተፍ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡

- የድምፅ መስጫ ወረቀትዎን በፖስጣ ቤት መላክ ይችላሉ -- የመላኪያ ፓስታው የቅድሚያ ክፍያ ስለተደረገበት ቴምብር አያስፈልገውም!
  - የድምፅ መስጫ ወረቀትዎ ላይ ፊርማና ቀን ማስፈርዎን ያረጋግጡ።
  - የድምፅ መስጫ ወረቀትዎ ከምርጫው ቀን በፊት ወይም በዕለቱ የፖስታ ቴምብር እንዳለው ያረጋግጡ።
- በካውንቲዎ ውስጥ በሚገኝ የትኛውም የምርጫ ጣቢያ ድምፅ የሰጡበትን ሰነድ (ፓስታ) ያስገቡ።
  - የምርጫ ጣቢያዎችን ከካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት ድረ ገጽ ማግኘት ይችላሉ ወይም በሚኖሩበት አካባቢ ያለን የምርጫ ጣቢያ አድራሻ ለማግኘት ይህንን ድህረ ገጽ ይጠቀሙ፡ sos.ca.gov/elections/polling-place
  - እስከ ምርጫው ቀን ድረስ ባሉት ሳምንታት ውስጥ የምርጫ ወረቀትዎን ማስገባት የሚችሉባቸው አስተማማኝ "የምርጫ ሳጥኖች" ዝግጁ ሊሆኑ ይችላሉ።

## በአካል ቀርበው ድምፅ መስጠትም ይችላሉ

በአካል ቀርበው ድምፅ ለመስጠት ከፈለጉ፣ ይችላሉ! ሒደቱን በተቻለ መጠን ቀላል ለማድረግ፣ የድምፅ መስጫ ሰነዶች በፓስታ ቤት ደርሶዎት ከሆነ ወደ ምርጫ ጣቢያው ይዘው ለመምጣት ይሞክሩ።

የምርጫው ቀን **ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 3/2020** ነው። የምርጫ ጣቢያዎች ከጥዋቱ **7 a.m. እስከ ምሽቱ 8 p.m ክፍት ሆነው ይቆያሉ።** እስከ ምሽቱ 8pm ድረስ ወረፋ ላይ ከተገኙ፣ ድምፅዎን መስጠት ይችላሉ።

**አብዛኞቹ ካውንቲዎችም ከቅዳሜ፣ ኦክቶበር 31/2020 ጀምሮ በአካል ድምፅ የመስጠት ዕድል ይሰጣሉ።** ሁኔታውን በአካባቢዎ ካለው የምርጫ ጽ/ቤት ያጣሩ።

ወደ ምርጫ ጣቢያው ሲሄዱ፣ መግቢያው አካባቢ ወደ አለው ጠረቤዛ በመሄድ ለምርጫ ጣቢያው ሰራተኞች ስምና አድራሻዎን ያሳውቁ። ከእንግሊዝኛ ውጭ በሌላ ቋንቋ ድምፅ ለመስጠት ከፈለጉ፣ በዚያ ቋንቋ የተዘጋጁ ሰነዶች እንዳላቸውና ከምርጫ ጣቢያው ሰራተኞች መካከል ያንን ቋንቋ የሚናገሩ መኖራቸውን ይጠይቁ።

### ድምፅ ለመስጠት ወደ የትኛው የምርጫ ጣቢያ መሄድ አለብኝ?

እርስዎ የተመደቡበትን የምርጫ ጣቢያ ከምርጫው በፊት ከካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት በተላኩልዎ ስነዶች ላይ ማግኘት የሚችሉ ሲሆን በተጨማሪም ይኽንን አስፈንጣሪ በመጫን የትኛው የምርጫ ጣቢይ መሄድ እንዳለብዎ ማጣራት ይችላሉ፡ sos.ca.gov/elections/polling-place.

### በየ ምርጫ ጣቢያወች የማህበረሰብ ጤና ጥበቃዎች ይደረጋሉን?

አዎ። የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች የፊት መሸፈኛ ጭምብል ወይንም ማስክ የሚያደርጉ ሲሆን የማህበረሰብ ጤና መመሪያዎችንም ሙሉ በሙሉ ይከተላሉ፣ አካላዊ መራራቅን በሚፈጥር መልኩም የምርጫ ጣቢያዎችን ያደራጃሉ። መራጮች የግዛትና የአካባቢ የማህበረሰብ ጤና ግዴታዎችን ማክበር ያለባቸው ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ የፊት መሸፈኛ ጭምብል ማድረግና አካላዊ ርቀትን መጠበቅ ይገኙበታል።

### ድምጽ በሚሰጥበት ጊዜ መታወቂያዬን ማሳየት ያስፈልገኛል?

በጣም ብዙ አጋጣሚዎች ላይ መታወቂያ ካርድ ማሳየት አይጠበቅብዎትም። ሰነዶች ማሳየት የሚኖርብዎት ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፅ እየሰጡ ከሆነና ለመራጭነት ሲመዘገቡ ነው። የመታወቂያ ካርድ የሚጠየቁት አዲስ መራጭ ሆነው ሲመዘገቡ የመንጃ ፈቃድዎን ፣ የግዛት መታወቂያዎን ወይንም የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርዎን ካላስመዘገቡ ብቻ ነው። ቀደም ብለው የተመዘገቡ ከሆነ፣ ሌሎች ሰነዶችም ተቀባይነት ይኖራቸዋል። ጉዳዩ ካሳሰበዎት፣ አስቀድመው ለምርጫ ጽ/ቤትዎ ደውለው ያጣሩ።

### ወደ ምርጫ ጣቢያው ሊያግዘኝ የሚችል ሰው ይዤ መሄድ እችላለሁ?

አዎ። በካሊፎርኒያ ሕግ መሰረት፣ በአካል ድምፅ ለመስጠት የሚያግዙዎት እስከ ሁለት የሚደርሱ ሰዎችን ይዘው መምጣት ይፈቀድልዎታል፤ ሰዎቹ ግን የሚሰሩበትን ቦታ ወይም የሰራተኛ ማህበርዎን የሚወክሉ መሆን የለባቸውም። የቤተሰብዎን አባል ወይም ጓደኛዎን ይዘው ወደ ምርጫ ጣቢያ መሄድ ይችላሉ።

## ከእንግሊዝኛ ውጭ በሌላ ቋንቋ ድምፅ ለመስጠት እችላለሁ?

የቋንቋ እገዛ በተመለከተ የሚሰጠው አገልግሎት እንደየካውንቲው ይለያያል። ድምፅ የሚሰጡት በፖስታ ቤት በኩል ከሆነ፣ እርስዎ ባሉበት ካውንቲ ውስጥ እርስዎ በሚመርጡት ቋንቋ ምን የተዘጋጀ ነገር እንዳለ ለማወቅ ለካውንቲዎ የምርጫ ጽ/ቤት ይደውሉ። ድምፅ የሚሰጡት በምርጫ ጣቢያ ከሆነ፣ የተተረጎሙ ሰነዶች መኖራቸውንና በቦታው የሚገኙ ሰራተኞች እርስዎ የመረጡትን ቋንቋ የሚናገሩ መሆናቸውን ይጠይቁ። በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉ ምልክቶችንም መፈለግ ይችላሉ።

እርስዎ በሚኖሩበት ካውንቲ ሊቀርቡ ከሚችሉ ቋንቋዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡ አረብኛ፣ አርሜኒያን፣ ቤንጋሊ፣ በርሚዝ፣ ቻይንኛ፣ ፋርሲ፣ ጉጃራቲ፣ ሂንዲ፣ ሂሞንግ፣ ኢልካኖ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ጃፓንኛ፣ ክሜር፣ ኮሪያኛ፣ ላኦ፣ ሚየን፣  ሞንጎሊያን፣ ኔፓሊ፣ ፑንጃቢ፣ ስፓኒሽ፣ ሴሪያን፣ ታጋሎግ፣ ታሚል፣ ቴሉጉ፣ ታይ፣ ኡርዱ እና ቬትናምኛ ይገኙበታል።

በካውንቲዎ ውስጥ ያሉትን ቋንቋዎች የሚያስረና በድምፅ አሰጣጥ ወቅት የሚኖርን ከቋንቋዎች ጋር የተያያዘ መረጃ ለማግኘት ይኽንን አስፈንጣሪ በመጫን መመልከት ይችላሉ፡  advancingjustice-alc.org/know-your-voting-rights.

### ድምፅ በምሰጥበት ወቅት ችግር ቢያጋጥመኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

አይደናገጡ! ዳግም ለመመዝገብና ድምፅ ለመስጠት **የተመሳሳይ ቀን የመራጬ ምዝገባ ለመጠቀም ይጠይቁ።** በሆነ ምክንያት ይህን ማድረግ ካልቻሉ፣ ጊዜያዊ የድምፅ መስጫ ወረቀት እንዲሰጥዎ ይጠይቁ፤ የምርጫ አስፈጻሚዎች የእርስዎን ብቁነት ካረጋገጡ፣ ይህ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከምርጫው ቀን በኋላ የሚቆጠር ይሆናል።

ወይንም፣ ከሚከተሉት የምርጫ ቀን የመራጬች ጥበቃ የስልክ መስመሮች በአንዱ ይደውሉ፡

- በእንግሊዝኛ ቋንቋ እገዛ ለመጠየቅ፡ 866-687-8683
- በእንግሊዝኛ፣ ማንዳሪን፣ ካንቶኒዝ፣ ቬትናምኛ፣ ኮሪያን፣ ቤንጋሊ፣ ኡርዱ፣ ሒንዲ እና ታጋሎግ ቋንቋዎች እገዛ ለመጠየቅ፡ 888-274-8683
- በእንግሊዝኛና በስፓኒሽ ከክፍያ ነጻ እገዛ ለመጠየቅ፡ 888-839-8682 ይደውሉ።